# አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን

# ሕዝባዊ ንቅናቄ

[ethiopiachen2009@gmail.com](mailto:ethiopiachen2009@gmail.com) , [info@ethiopiachen.org](mailto:info@ethiopiachen.org)
[www.ethiopiachen.org](http://www.ethiopiachen.org), [www.ethiopiachen.com](http://www.ethiopiachen.com)

መስከረም ፰ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ.ም. (September 18, 2016)

## ጋዜጣዊ መግለጫ

## እኛም ለሀገራችን

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት በየቦታው ከዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ጋር እየተፋለመ ይገኛል። ኢትዮጵያውያን 2009 ዓ.ም. የአዲስ ዘመን መለወጫ በዓል በሀዘንና በለቅሶ የተቀበሉት የደረሰባቸውን የ25 ዓመት የመከራና የግፍ አገዛዝ ማብቃት እንዳለበት ከምንግዜውም በላይ ቆርጠውና ታጥቀው መነሳታቸውን ጠቋሚ ነው። ሕዝባችን የወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግን አገዛዝ ለማስወገድ በሰላማዊ ትግሉ መስከ በምርጫ 1997 ዓ.ም. ማንነቱን አሳይቷል። የወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ አምባገነን ገዥዎች ያጠለቁት የዴሞክራሲያ ጭምብል እርቃኑን የወጣበት ወቅት ቢኖር ምርጫ 1997 ዓ.ም. ነበር። የሕዝብ የበላይነትና የሕዝብ ድምጽ ላለመቀበል ዘረኛው የወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ መሣሪያ አንስቶ ንፁሃን በአደባባይ የፈጀበት ወቅት 1997 ዓ.ም. እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። በተለይ ከ1997 ዓ.ም. የምርጫ ትርዕይት ወዲህ ወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ በመሣሪያውና በጉልበቱ ሕዝብን አፍኖ ሊገዛ ሞክሯል። በየጊዜውና በተለያየ አካባቢ የተነሱ መለስተኛ ሕዝባዊ ጥያቄዎችን በኃይልና በጉልበት ሊያንበረክክ የሞከረው የወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ዛሬ ዳር እስከ ዳር በሕዝባዊ እምቢተኝነት ወጥመድ ውስጥ ተዘፍቆ ይገኛል።

ከታሪክ መማር የተሳነው ወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ ያነገበው የጦር መሣሪያ ከሕዝብ ኃይል ሊበልጥ እንደማይችል አለመገንዘቡ የአምባገነን ባህሪው መገለጫ ነው። ቢገነዘብም ሀገርና ሕዝብ ሊያጠፉ ጥንስስ እቅዱ የነበረው ወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ የጦር መሣሪያውን ንፁሃን ወገኖቻችን ላይ እያርከፈከፈ ይገኛል። ዛሬ ሕዝብ ሀገሩንና አንድነቱን ሊከላከል በአንድ በኩል፤ የወንበዴው ወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ሀገርን ሊበታትንና ሕዝብን ሊያጠፉ በሌላ በኩል ፍጥጫው ከሯል። በወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ የዘረኝነት አገዛዝ ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ቀላል ሊሆን እንደማይችል ቢገመትም መብቴንና ሀገሬን ብሎ የተነሳው ሕዝብ የመጨረሻው አሸናፊ እንደሚሆን የማንጠራጠረው ታሪክን ዞር ብለን ስለምንመለከት ነው።

ዛሬ በሀገራችን ኢትዮጵያ የተፋፋመው ሕዝባዊ ንቅናቄ በወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ ተሸናፊነት ብቻ ማብቃት ሳይሆን በሕዝብ የበላይነት መመራት ይኖርበታል። በአሁኑ ወቅት በተለያዩ አካባቢዎች

የተነሳሳውን ሕዝባዊ ንቅናቄ ተገን አድርገው አሁንም የሀገራችን መበታተንና የሕዝባችን የእርስ በርስ ግጭት ናፋቂዎችን ለዳግም የዘረኝነት አገዛዝ በሩ እንዳይከፈት “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” እኛም ለሀገራችን፣ እኛም ለሕዝባችን ዴሞክራሲያዊ አንድነት ብለን ክንዳችንን አንስተናል። ከእምዬ ኢትዮጵያና ከሕዝባችን ጐን “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!” ብለን ተሰልፈናል። ትግሉ ተገቢውን አቅጣጫ እንዲይዝና ኢትዮጵያ ሀገራችን አንድነቷን ጠብቃ የሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች ሀገርና የዜግነት መብት የተከበረባት አዲሲቷ ኢትዮጵያ ግንባታ ላይ አማራጫችንን ይዘን ለሕዝብና ለሀገር ብቅ ብለናል።

*ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!*

ለአንድ ዓመት ያህል አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶችን ስናደርግ ቆይተን “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” መስከረም 6, 7 እና 8 ቀን 2009 ዓ.ም. (September 16-18, 2016) በአደረግነው የመጀመሪያ ጉባኤ የንቅናቄውን መመስረት ልናበስር እንወዳለን። በመሆኑም ከዚህ ጋዜጣዊ መግለጫ ጋር የንቅናቄውን ድርጅታዊ ፕሮግራም በዛሬው ቀን ለሀገራችንና ለሕዝባችን ስናቀርብ በታላቅ ደስታ ነው። ጉባኤው በተለያዩ ወቅታዊ የሀገራችን ጉዳይ ላይ ሠፊ ውይይት ከአደረገ በኋላ የውስጥ መተዳደሪያ ደንቡን በማጽደቅ፣ የንቅናቄውን አመራር አካል በመሰየምና ፕሮግራሙን ለሕዝብ ይፋ እንዲሆን በመወሰን እነሆ በሕዝባዊ ትግሉ ውስጥ ታጋይና አታጋይ ለመሆን ቃል ገብተናል።

ቀደም ሲል ለአስተያየት የተበተነው “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” ማንፌስቶ በአገኘነው አስተያየት መሠረት ተሻሽሎ ማታገያ ሠነድ ይሆን ዘንድ በድረ ገፃችን ላይ እንዲለጠፍ ጉባኤው ወስኗል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በዛሬው ቀን የንቅናቄው ድረ ገጽ www.ethiopiachen.org እና www.ethiopiachen.com ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ አድርገናል።

የ“አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” ልሳን “ኢትዮጵያችን” መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለማሳወቅ እንወዳለን።

*ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብና በመላው ዓለም ለምትገኙ ወገኖቻችን!*

የ”አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” ዓላማ ኢትዮጵያ ሀገራችን የግዛት ሉዓላዊነቷን ጠብቃ የሁሉም ዜጐቿ ያልተሸራረፈ መብት የሚከበርባትና ሁሉም ሀገሬ ብሎ ወደ ልማትና ዕድገት ጎዳና ፊቱን አዙሮ የሥልጣኔ አውራ የነበረችውን ኢትዮጵያ የተለያዩ ባህሎቿን፣ ቋንቋዎቿን፣ ጐሳዎቿን፣ ሃይማኖቶቿን ይዛ ዴሞክራሲያዊ አንድነቷን ጠብቃ ሕዝቧን መግባ ወደ ሥልጣኔ ጎዳና እንድታመራ አቅጣጫ ለመስጠት የድርሻችንን ለማበርከት ተነስተናል።

ዛሬ መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕዝብ በየቦታው የተያያዙት ፀረ-ወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ ትግል አቅጣጫውን እንዳይስትና ሕዝባዊ ትግሉ በሕዝባዊ ድል ይጠናቀቅ ዘንድ ሊከፈል ሚችለውን የሕይወት መስዋዕትነት በመክፈል የራሳችንን አስተዋጽዎ ለሀገራችንና ለሕዝባችን ለማበርከት ቃል የገባንበት ቀን ነው።

በዚህ “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” ቀጣይ ሂደት ለኢትዮጵያ የግዛት ሉዓላዊነትና ለሕዝቧ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ከሚታገሉ ፀረ-ወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ ኃይሎች ጋር በጋራ ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመሥራትና ለመተባበር ያለንን አቋም ግልጽ ለማድረግ እንወዳለን።

**ትላንትም ዛሬም ወደፊትም ኢትዮጵያ ለዘለዓለም እንድትኖር፣ ለሕዝቧና ለልጆቿ የሆነች አዲሲቷን ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ የሁሉንም ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ ድጋፍና ትብብር እንጠይቃለን።**

የ"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!" ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" ማንፌስቶ ላይ ባስቀመጥነው መሠረት አዲስ የፖለቲካ ድርጅት ሊመሠረት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት፡-

- በኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ላይ ከማንም ሳንደራደር "አንድ ኢትዮጵያ" ብለን በመነሳታችን
- ኢትዮጵያ የሁሉም ዘሮች፣ ብሔር/ብሔረሰቦች ሀገር መሆኗን ተቀብለን ሁሉንም በእኩልነት የምትመለከት "አንድ ሕዝብ" ብለን መነሳታችን
- በውጭው ዓለም የሚደረጉ ዲፕሎማሳዊ እንቅስቃሴዎችና በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን ለትግሉ የሚያበረክቱት እገዛ እንደተጠበቀ ትግሉን ሙሉ በሙሉ በሀገር ቤት በማድረግና እንቅስቃሴውንም እዚያው በሀገር ቤት ያሉት ወጣቶችና ጎልማሶች በአጠቃላይ የአሁኑ ትውልድ ኃላፊነቱን እንዲረከብ ለማድረግ
- በተለይ በአለፉት አርባ ዓመታት የትግል ታሪክ የአገዛዝ ሥልጣናቸውን ተገን አድርገው የሀገር ሀብትና ንብረት የዘረፉ፣ የሕዝብ ልጆችን ሕይወት የቀጠፉ ወንጀለኞች ከወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ ውድቀት በኋላ በሚደረገው ብሔራዊ ዕርቅ በሀገርና ሕዝብ ላይ የደረሰውን በደል እውቅና ሰጥቶ መዳኘ የሚቻልበትን አቅጣጫ ለመቀየስ
- የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በባህል፣ በሃይማኖት፣ በአኗኗር የተሳሰረ ቢሆንም ወያኔና ሻቢያ በፈጠሩት የሀገር መበተን አጀንዳ ኤርትራ ተገንጥላለች። በንቅናቄው ሠነድ መሠረት ወያኔና ሻቢያ የኢትዮጵያና የሕዝባችን ጠላቶች በመሆናቸው ቀጣዩ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ መሠረት ለኤርትራ እንደ ሀገር እውቅና ከሰጠ ከኤርትራው አምባገነን ገዥና ሻቢያ ጋር የሚኖረው ግንኙነት እጅግ ጥንቃቄ የተሞላበት መሆን ስለሚገባው
- ኤርትራ በሻቢያና በወያኔ የጋራ ስምምነት ያለአግባብ የወሰደችውን አሰብ ወደብ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለኢትዮጵያ መመለስ እንደሚኖርባት የሚሞግት ፖለቲካ ድርጅት አስፈላጊ በመሆኑ
- ለትውልድ የሚተላለፍ ዘለቄታዊ ሕገ መንግሥት ለማርቀቅና ተግባራዊ ለማድረግ ለሚደረገው አስተዋጽዎ የኢትዮጵያንና የሕዝቧን አንድነት ለማስረገጥና በታሪክ ጠባሳ ጥሎ ላለማለፍ የዜግነት ግዴታን መወጣት ስለሚያስፈልግ
- ከወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ ውድቀት በኋላ ለተወሰነ ዓመታት ሀገሪቷ በጋራ አመራር ትዳዝ ዘንድ በቀረበው በንቅናቄው ሠነድ መሠረት በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና እንዲሁም ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ የጋራ ኅብረት ስምምነት ይፈጠር ዘንድ አስተዋጽዎ ማድረግ በማስፈለጉ
- በመጨረሻም አሁን በአገራችን እየተካሄደ ያለው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አመራር አጥቶ ወደ አላስፈላጊ አቅጣጫ እንዳይዳዝ ለትግሉ ያለውን የአመራር ክፍተት ከሌሎች ታጋይ ኃይሎች ጋር ለመሸፈን ጥረት ማድረግ በማስፈለጉ

"አንድ ሕዝብ! አንድ ሀገር! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" የፖለቲካ ድርጅት መቋቋሙን ልናበስር ወደድን።

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**
**እግዚሃብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**
**"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ሕዝባዊ ንቅናቄ"**

**ኢሜል፡** ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
**ድረ ገጽ፡** www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com